# ደንብ IKA-RA፦ ስለ ውጤት አሰጣጥ እና ሪፖርት ማድረግ ማሻሻያ
# 2025-2026 የትምህርት ዓመት

ለምን?

| | | |
|---|---|---|
| ተማሪዎች ጠንክረው እንዲሠሩ እና ተጠያቂነትን ለማስፈን | በተለያዩ ትምህርት ቤቶች ያለውን የተራራቀ ልዩነት ለማጥበብ | የሚጠበቁ የሥራ ውጤቶችን ግልጽ ለማድረግ |

የተለወጠው ነገር ምንድነው?

- **የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት/ኮርስ የውጤት አሰጣጥ ስሌት፦** ከ 6ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ተማሪዎች በሙሉ አዲስ የማጠቃለያ ውጤት አሰጣጥ ስሌት ይተገበራል። ከ 2025-2026 የትምህርት አመት ጀምሮ፣ የመጨረሻው የኮርስ ውጤት የሚወሰነው በእያንዳንዱ የማርክ መስጫ ወቅት በቁጥር የተሰጡ ውጤቶችን አማካይ ውጤት በማስላት ነው። መምህራን በፊደል የሚጻፈውን የመጨረሻውን ውጤት ለመወሰን ከዚህ በኋላ የስሌት ሠንጠረዥ አይጠቀሙም።
  - በሴሚስተር ለሚጠናቀቁ ኮርሶች፦ የመጨረሻውን ውጤት ለማስላት ከሁለቱም የማርክ መስጫ ወቅቶች አሃዛዊ ውጤቶችን ድምር ለሁለት በማካፈል አማካኝ ውጤት ይወሰዳል።
  - የሙሉ አመት ኮርሶች፦ የመጨረሻው ውጤት የሚሰላው የአራቱንም የማርክ መስጫ ወቅቶች በቁጥር የተጻፉ የማርክ ውጤቶችን በመደመር እና በአራት በማካፈል አማካዩ የማጠቃለያ ውጤት ይሆናል።
  - የኮርስ ማጠናቀቂያ (EOC) ፈተና ውጤት፦ የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ዲፓርትመንት (MSDE) በባዮሎጂ እና NSL Gov't የመጨረሻ የኮርስ ምዘና የሴሚስተር B ውጤት 20% ይይዛል።

- **የማርክ መስጫ ወቅቶች (MP) 2 እና 4 የማጠቃለያ ግምገማ፦** የተወሰኑ ትምህርቶችን በሚመለከት ዲስትሪክት አቀፍ የማጠቃለያ ግምገማዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ። MP 2 እና MP 4 ምዘናዎች 10% ይቆጠራል። ወደፊት የኮርሶቹ ዝርዝር ይወጣል።

- **የሪፖርት ካርዶች፦** አዲሱን የተማሪዎች የትምህርት አፈጻጸም ሪፖርት ለማድረግ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የሪፖርት ካርድ ይሻሻላል።

- **ድጋሚ ግምገማ፦** በሁሉም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ኮርሶች፣ ምድብ መምህራን በእያንዳንዱ ማርክ መስጫ ወቅት ለተማሪዎች ቢያንስ ሁለት ዙር የግምገማ እድሎችን ይሰጣሉ። ነገር ግን የሚከተሉት ምዘናዎች እንደገና ሊገመገሙ አይችሉም፦ የኮርስ ማጠቃለያ ምዘናዎች፣ የማርክ መስጫ ክፍለጊዜ ግምገማዎች፣ ተፈላጊ የዲስትሪክት ግምገማዎች፣ የሴሚስተር ማጠቃለያ ግምገማዎች፣ የመጨረሻ የምርምር (የሪሰርች) ጽሑፎች፣ ፕሮጀክቶች ወይም ጽሑፎች፣ እና የማጠናቀቂያ ፕሮጀክቶች ወይም የማጠናቀቂያ አፈፃፀሞች ዳግመኛ ምዘና አይኖራቸውም።

- **የመጨረሻ ቀናት እና ቀነገደቦች፦**
  - የማስረከቢያ ቀን የመጨረሻው ቀነገደብ ከ 10 የትምህርት ቀናት በላይ ሊሆን አይችልም።
  - ወቅቱን ጠብቆ የውጤት ሪፖርት ለመስጠት አስቸጋሪ ስለሚሆን፣ እያንዳንዱ የማርክ መስጫ ክፍለጊዜ ከማብቃቱ በፊት እስከ መጨረሻዎቹ 5 የትምህርት ቀናት ዘግይቶ የሚቀርብ ስራ ተቀባይነት አይኖረውም።

- **50% መመደብ፦** የተማሪዎች የስራ ውጤት ወይም ትክክለኛነት ምንም ይሁን ምን መምህራን በሚገመግሟቸው መመዘኛዎች ላይ ከ 50% በታች ውጤት መስጠት የለባቸውም። መምህራን ድጋፍ መስጠት እና ጣልቃ ገብተው በማስተማር እገዛ ማድረግ ይቀጥላሉ።

- **የተማሪዎችን የስራ ውጤት መመለስ፦** የተማሪዎች የሥራ ውጤት በ 10 የትምህርት ቀናት ውስጥ ለተማሪዎች ይመለሳል።

ቀደም ሲል ማሻሻያ የተደረገበት ቀን፡ 06/11/2025